## ው ሣ ኔ

1/ የፌ/ከ/ፍ/ቤት በመ/ቁ.36910 በመጋቢት 15 ቀን 1998 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ እና የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 33322 ሐምሌ 6 ቀን 1996 ዓ.ም የሰጠው ብይን መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመባቸው በመሆናቸው ተሽረዋል፡፡ ይፃፍ፡፡

2/ የፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ በዚህ መዝገብ የቀረበውን ክርክር አይቶ የመወሰን ስልጣን የሌለው በመሆኑ ክርክሩ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 5 መሠረት በድጋሚ ቀርቧል ሊባልም ሆነ ፍ/ቤቶች ስልጣን የላቸውም ለማለት ባለመቻሉ በግራ ቀኙ ክርክር የተነሱ ሌሎች መቃወሚያዎችን እና የፍሬ ነገር መከራከሪያዎችን መርምሮ የመሠለውን እንዲወስን ጉዳዩ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 341 መሠረት ለፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ይመለስለት ብለን ወስነናል፡፡ ይፃፍ፡፡

3/ ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡

4/ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ተ.ወ



የሰ/መ/ቁ.24775

ጥቅምት 21 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- አብዱልቃድር መሐመድ
ተገኔ ጌታነህ
መስፍን ዕቁበዮናስ
ተሻገር ገ/ስላሴ
ብርሃኑ አመነው

አመልካች- ማታዶር አዲስ ጎማ - ጠበቃ - አቶ ደረጀ ታፈሰ ወርቁ፡፡

ተጠሪ፡- ቢተው ረታ - ቀረቡ፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፈርደናል፡፡

## ፍ ር ድ

ተጠሪ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በአመልካቹ ላይ ለተመሠረተው ክስ አመልካች መልስ ይዞ እንዲቀርብ ፍ/ቤቱ በያዘው ቀጠሮ አመልካች ቀርቦ መልስ ባለመስጠቱ ጉዳዩ በሌለበት እንዲታይ ታዟል፡፡ ፍ/ቤቱ ትዕዛዙን እንዲያነሳለት አመልካች ያቀረበውን ማመልከቻም ፍ/ቤቱ ባለመቀበሉ ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ቀርቦ ይግባኙ አያስቀርብም በመባሉ አመልካች ለዚህ ፍ/ቤት አቤቱታውን አቅርቧል፡፡

አቤቱታው ለሰበር ችሎት ያስቀርባል ተብሎ ተጠሪ ክርክሩን ለመስማት ቢጠራም ባለመቅረቡ ጉዳዩ በሌለበት ቀጥሏል፡፡ በዚህም አመልካች መልስ ስጥ በተባለበት ዕለት ባለመቅረቡ ጉዳዩ በሌለበት እንዲታይ የመታዘዙን ተገቢ መሆን ያለመሆን መርምረናል፡፡

የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 233 አንድ ተከሳሽ የመከላከያ መልሱን ፅፎ እንዲያቀርብ ታዞ መከላከያውን ለፍርድ ቤቱ ሳያቀርብ የቀረ ወይም ራሱ መከላከያ ሳይይዝ የቀረበ እንደሆነ ክርክሩ በሌለበት የሚሠማ መሆኑ በመጥሪያ ይገልፅለታል ይላል፡፡ ከዚህ መገንዘብ የሚቻለው አንድ ተከሳሽ በሌለበት ጉዳዩ እንዲታይ የሚታዘዘው መልስ እንዲያቀርብ በታዘዘበት ቀን ሲቀር ሣይሆን በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 241 መሠረት ክርክሩ ሊሠማ በተቀጠረበት ቀን ያልቀረበ

እንደሆነ ነው፡፡ የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.241/1/ "ክሱ መሠማት በሚጀምርበት ቀን.....ቀርቦም እንደ ሆነ የመከላከያውን መልስ ለግራ ቁኙ" ፍ/ቤቱ እንደሚያነብ መጥቀሱ አንድ ተከሳሽ መልስ ባያቀርብ እንኳን ክሱ ሲሠማ በተቀጠረበት ዕለት ቀርቦ መከራከር እንደሚችል የሚያሣይ ነው፡፡ በመሆኑም አመልካች መልስ እንዲያቀርብ በታዘዘበት ዕለት ባለመቅረቡ ብቻ የሥነ ሥርአት ሕጉን ያላግባብ በመተርጎም በሌለበት ጉዳዩ ይታያል መባሉ መሠረታዊ የመሰማት መብቱን የገደበ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

**<u>ው ሣ ኔ</u>**

የሥር ፍ/ቤቶች አመልካች መልስ እንዲሠጥ በታዘዘበት ዕለት ባለመቅረቡ በሌለበት እንዲታይ መወሰናቸው መሠታዊ የሕግ ስህተት በመሆኑ ውሣኔዎቹ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.348/1/ መሠረት ተሽረዋል፡፡

የፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት በሕጉ መሠረት የግራ ቀኙን ክርክር ሰምቶ ተገቢውን እንዲወስን ታዟል፣ይፃፍ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቤ/ኃ



የሰ/መ/ቁ. 25026

ግንቦት 14 ቀን 2000 ዓ.ም.

ዳኞች፡- አብዱልቃድር መሐመድ

ታፈሰ ይርጋ

መድኅን ኪሮስ

ዓሊ መሐመድ

ሱልጣን አባተማም

አመልካች፡- ወ/ሮ ሁዳ መሐመድ - ጠበቃ አቶ ይልማ አቻሜ ቀረበ፡፡

ተጠሪ፡- ሀጂ አህመድ አህመዲን፣ ጠበቃ ደምሴ ኪዳኔ ቀረቡ፡፡

መዝገቡን የተቀጠሪው፣ ለምርመራ ነበር፡፡ መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**<u>ፍ ር ድ</u>**

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሚያዝያ 6 ቀን 1998 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት የሰበር አቤቱታ በማቅረቡ ነው፡፡ የክርክሩን ፍሬ ጉዳይ በተመለከተ፣ አመልካች ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በከሳሽነት ቀርባ ከተከሳሽ ጋር ታህሣሥ 8 ቀን 1991 ዓ.ም. በተደረገ የቤት ሽያጭ ውል፣ በአዲስ አበባ ከተማ ወረዳ 6 ቀበሌ 02 ክልል የቤት ቁጥር 003 የሆነው ቤት በብር 650,000 /ስድስት መቶ ሀምሣ ሺህ ብር/ ገዝቼአለሁ፡፡ በዚህ ጊዜ ብር 70,000 /ሰባ ሺህ ብር/ የመጀመሪያ ክፍያ የከፈልኩ ሲሆን የቤቱን ካርታ እና የባለቤትነት ደብተር ማረጋገጫ ተረክቤአለሁ፡፡ ተከሣሽ በውሉ መሠረት እንዲፈጽም ማስጠንቀቂያ ብሰጠው ፈቃደኛ ስላልሆነ፣ በፍርድ ተገድዶ ቤቱን እንዲያስረክብና የውል ግዴታውን እንዲፈጽም ውሣኔ ይሰጥልኝ በማለት ክስ ያቀረበች ሲሆን፣ ተጠሪው የከፍተኛው ፍርድ ቤት መጥሪያና ክስ ደርሶአቸው መልሳቸውን፣ ይዘው ባለመቅረባቸው ጉዳዩ በሌሉበት እንዲታይ የከፍተኛው ፍርድ ቤት ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡ ተጠሪው ፍርድ ቤቱ በሌለበት እንዲታይ ትዕዛዝ ከሰጠ ከሶስት ወር በኋላ ወደ ክርክሩ ለመግባት እንዲፈቀድለት የጠየቀ